## ተቋሙ በአዋጅ ሲቋቋም ከተሰጠው ዋና ዋና ተግባራት መካከል ባለፉት ዓመታት ያከናወናቸውን እና እያከናወናቸው ያሉትን የተግባራት ክንውንን ስንመለከተ

ተቋሙ ከተቋቋመ ጀምሮ በርካታ ስልጠናዎችን ሲያስተባብር እና ሲሰጥ ቆይቶል፡፡ ነገር ግን ከ2007 ዓ/ም በፊት ተቋሙ ምንም እንኳን የራሱ የሆኑ ችግሮች ቢኖሩበትም መደበኛ ስራቸው ስልጠና መስጠት እና ጥናትና ምርምር የሚያካሄዱ ባለሙያዎችን ቢቀጥረም ሴ/መ/ቤቶች የተቋሙን አሰልጣኞች ከመጠቀም እና ስልጠናዎች በተቋሙ ውስጥ ከመስጠት ይልቅ በሌሎች ቦታዎች ሲሰጡ ቆይቷል፡፡ ነገር ግን ከ 2008ዓ/ም ጀምሮ ግን በፊት ከነበረው በተጠናከረ መልኩ የተቋሙ የቦርድ አባላት ተቋሙ የተሰጠውን ተግባርና ሀላፍነት በአግባቡ እንዲወጣ እና የሚገጥሙትን ተግዳሮቶች በወቅቱ እንዲፈታ እና የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በመቆጣጠር፣ በማስተዳደር እና በመገምገም አቅጣጫ እንዲሰጥ አድርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማር የክልሉ መንግስት በተለያዩ ጊዜያት ማንኛውም ስልጠና በተቋሙ ብቻ እንዲሰጥ አቅጣጫ ቢያስቀምጥም ከአንዳንድ ሴክተር መስሪያ ቤቶች በስተቀር በአብዛኛው በክልሉ የሚገኙ ሴ/መ/ቤቶች ተቋሙ በሚሰጣቸው እና በሚያስተባብራቸው ስለጠናዎች ተቋሙን እየተጠቀሙ አለመሆናቸውን ተቋሙ በተለያዩ ገዚያት ባካሄደው የዳሰሳ ጥናት ለማረጋገጥ ተችልዋል፡፡ በዚህም መሰረት ተቋሙ በየበጀት ዓመቱ ክልል አቀፍ የስልጠና ፍላጎት በሶስት ዞኖች እና በተመረጡ ወረዳዎች እና በክልል ሴክተር መ/ቤቶች ጥናት አካሂዶ በተገኘው የጥናት ውጤት መሰረት በተለያዩ የስልጠና ርዕሶች እና ተጨማሪ አዳዲስ የስልጠና ርዕሶችን በማካተት በየአመቱ በክልሉ ለሚገኙ ሁሉም ተቋማት መረሀ-ግብር በማዘጋጀት እያሰራጨ እና እያስተዋወቀ ይገኛል፡፡በተጨማሪም ተቋሙ በአዋጅ ከተሰጠው ዋና ዋና ተግባራት መካከል በክልሉ በሚገኙ ተቋማት ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማካሄድ ሲሆን በተለይም ከ2007ዓ/ም ጀምሮ ቦርዱ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት አቅም እና ልምድ ያላቸውን አማካሪዎች ወደ ተቋሙ በመቀላቀላቸው የተሻሉ ጥናትና ምርምር ስራዎች እንዲካሄዱ ተደረጓል፡፡ ከተካሄዱት የጥናትና ምርምሮች ርዕስ መካከል የሚከተሉትን ማንሳት ይቻላል፡- በቤ/ጉ/ክ/መ የጤና ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ የደንበኞችን እርካታ ደረጃ ለመለየት የተካሄደ ጥናት፤

- በቤ/ጉ/ክ/መ በተቋማት በጀት አጠቃቀም ላይ ተጽእኖ የሚያስከትሉ ተግዳሮቶችን መለየት፤
- በቤ/ጉ/ክ/መ ሰፋፊ የእርሻ ኢንቨስትመንት ለአከባቢ ማህበረሰብ ያበረከተውን አስተዋጽኦ

ለመለየት የተካሄደ ጥናት፤

- በቤ/ጉ/ክ/መ ለመንግስት ሰራተኛው የሚሰጠው ስልጠና ለአገልግሎት ጥራት መሻሻል ያለውን አስተዋጽኦ ለመለየት የተካሄደ ጥናት፤
- በቤ/ጉ/ክ/መ ተቋማት ሴቶች ወደ አመራርነት እንዳይመጡ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተግዳሮቶችን ለመለየት የተካሄደ ጥናት፤
- በአሶሳ ፖሊ ቴክኒክ ትምርት እና ሥልጠና ኮሌጅ በተመራቂ ተማሪዎች ሥራ ፈጠራ ፍላጎት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተግዳሮቶችን ለመለየት የተካሄደ ጥናት፤
- በቤ/ጉ/ክ/መ የሰራተኞች የስራ ላይ እርካታ ደረጃ ለመለየት የተካሄደ ጥናት፤
- በቤ/ጉ/ክ/መ የጋራ ግዢ አፈጻጸም ውጤታማነት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተግዳሮቶችን ለመለየት የተካሄደ ጥናት፤ በቤ/ጉ/ክ/መ የሚገኙ ተቋማት የውጤት ተኮር ስረዓት ትግበራ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ለመለየት የተካሄደ ጥናት፤
- በቤ/ጉ/ክ/መ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ የዜጎች ቻርተር ትግበራ ያለበትን ደረጃ ለመዳሰስ የተካሄደ ጥናት፤
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት በአሶሳ ዞን የኮሮና ቫይረስ በሽታ መከላከያ ዘዴዎች ትግበራ ያለበትን ደረጃ ለመዳሰስ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት፤
- በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት የአመራር ዘይቤዎች በሠራተኞች የሥራ አፈፃፀምላይ ያላቸዉን አስተዋጽኦ ለመለየት የተካሄደ ጥናት፤